የሰ/መ/ቁጥር 36894

ታህሳስ 30 ቀን 2001 ዓ/ም

**ዳኞች ፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች ፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ  ነገረ ፈጅ ወ/ሮ ኮከብ ስለሺ

**ተጠሪ ፡-** አቶ ሙላት ታረቀኝ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 58378 በመጋቢት 8 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቀ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በከሳሽነት በመቅረብ ከታህሳስ ወር 1972 ዓ.ም ጀምሮ ተቀጥሮ በአመልካች ድርጅት ውስጥ የተለያየ ስራ ሲሰራ የቆየ መሆኑን ከገለፀ በኋላ ህዳር 23 ቀን 1998 ሃላፊነትህን አልተወጣህም የሚል ምክንያት በመስጠት አላግባብ ከሥራ ያሰናበተኝ ስለሆነ ፍርድ ቤቱ የሥራ ስንብቱን ውድቅ እንዲያደርግለት ጠይቋል፡፡ አመልካች በበኩሉ በተከሳሽነት ቀርቦ የይርጋ የጊዜ ገደብ አልፏል፣ የሚልና ተጠሪ ሰራተኛ ሳይሆን የሥራ መሪ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለውም የሚል መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን መቃወሚያ በመቀበል ተጠሪ የሥራ መሪ መሆኑን በመግለጽ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ዘግቶታል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ  ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ ምክትል የግምጃ ቤት ሐላፊ በመሆን ያገለገለው በጊዜአዊነት ስለሆነ በቋሚነት ተመድበው ያልሰሩበት የሥራ መደብ የሥራ መሪ ሊያሰኛቸው አይችልም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በአሠሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት አከራክሮ እንዲወሰን በማለት መልሶለታል፡፡ አመልካች ይኸ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ የሥራ መሪ ናቸው፡፡ በሥራቸውም የሚመሯቸውና የሚያስተደድሯቸው ሠራተኞች አሉ፡፡ በምክትል ግምጃ ቤት ሃላፊነት የተመደቡት በጊዜያዊነት ቢሆንም ሙሉ ሃላፊነቱን እና የሚያስገኘውን መብት ተረክበው እስከሰሩ ድረስ በጊዜያዊነት በመመደባቸው ብቻ ሠራተኛ አያደርጋቸውም፡፡ ስለዚህ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 377/1993 አንቀጽ 3/2/ሐ ድንጋጌና የህብረት ስምምነቱን አንቀጽ 14 የሚተላለፍ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ እኔ በቦታው ላይ ተመድቤ እየራ የነበረው በተጠባባቂነት ነው፡፡ የሰራተኛ ወገን እንጅ የአሰሪ ወገን አይደለሁም፡፡ አመልካች ለክርክር ያቀረበው የሥራ መዘርዝር ለእኔ ያልተሰጠኝና እኔ የማላውቀው ነው፡፡ አመልካች በመከራከሪያነት የሚጠቅሰው አስረኛውን የህብረት ስምምነት ሲሆን እኔ ሥራ ላይ በነበርኩ ጊዜ የነበረው ዘጠነኛው የህብረት ስምምነት ነው፡፡ በወቅቱ የሠራተኛ ማህበሩ ከፍተኛ ኃላፊ የነበርኩ ስለሆነ አመልካች ሥራ መሪ ነው ለማለት የሚያቀርበው ክርክር ተገቢነት የሌለው ነው፣ ስለዚህ ፍርድ ቤቱ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ያሰናብተኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በጽሑፍ የመልስ መልስ ያቀረበ ሲሆን፣ ይህ ችሎት የአመልካችንና የተጠሪን

የቃል ክርክር አዳምጧል፡፡ እንደዚሁም አመልካችና ሠራተኛ ማህበሩ የተስማሙበትን ዘጠነኛውን የህብረት ስምምነትና አስረኛውን የህብረት ስምምነት በማስቀረብ ተመልክቷል፡፡

በሥርና በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች የሥራ መሪ ነው ወይስ ሠራተኛ? የሚለው ነጥብ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ በተጠባባቂነት ተመድበው ይሰሩበት የነበረው የሂሳብ ክፍል ረዳት ኃላፊ የሥራ ቦታ ላይ የነበረ መሆኑና ተጠሪም የክፍሉን እንቅስቃሴዎች የመቆጣጠር የዕለት ከዕለት የሒሳብ ቁልፎችን መያዝና የሒሳብ ክፋዬችን የዕለት ተዕለት የሥራ ምደባ ፕሮግራም እንደሚያዘጋጅ ተጠሪ ተመድቦ ይሰራበት የነበረው የሥራ መደብ የሥራ መዘርዝር በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህም ተጠሪ የሰራተኛነት ሳይሆን የሥራ መሪነት የሥራ ድርሻ የነበረው መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ በተጠባባቂነት ተመድቦ ይሰራበት የነበረው የሥራ መደብ ተጠሪ በስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ተፈፃሚነት በነበረው ዘጠነኛ የሕብረት ሥራ ስምምነት መሠረት የሠራተኛ የሥራ መደብ ሣይሆን የሥራ መሪ የሥራ መደብ መሆኑ በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 10 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚህም ተጠሪ በተጠባባቂነት ተመድቦ ሲሰራበት የነበረው ምክትል የግምጃ ቤት /የሂሳብ ክፍል/ ኃላፊ የሥራ መደብ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 ንዑስ አንቀጽ 3/2/ሐ/ መሠረት የሥራ መሪ የሥራ መደብ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ በተጠባባቂነት የሚሰራበት የነበረው የሥራ መደብ የሥራ መሪ የሥራ መደብ ነው ከተባለ ተጠሪ በሥራ መደቡ ይሰራ የነበረው በቋሚነት ሳይሆን በተጠባባቂነት መሆኑ ተጠሪን ሰራተኛ ያሰኘዋል ወይስ አያሰኘውም? የሚለውን ነጥብ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ ተጠሪ በተጠባባቂነት ተመድበው ሲሰሩ ለቦታው የሚገባውን ጥቅማጥቅም የሚያገኙ እንደነበርና ለሥራው ሙሉ ሀላፊነት ወስደው ይሰሩ እንደነበር በስርና በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ያሳያል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 494/1998 ከተደረገው፣ ማሻሻያ መሠረት የሥራ መሪ ማለት በቋሚነት ብቻ ሣይሆን በአሠሪው በተሰጠው ውክልና መሠረት በአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2/ሐ/ የተዘረዘሩትን ተግባራት የሚያከናውን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ በቦታው ላይ ተመድበው ይሰሩ የነበሩት በተጠባባቂነት መሆኑ ተጠሪ ሠራተኛ ናቸው ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ ምክንያት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ከላይ የተገለፁትን የህግ ድንጋጌዎች ሳያገናዝብ ተጠሪ ሠራተኛ ነው የሥራ መሪ አይደለም በማለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 58378 መጋቢት 8 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 21891 ሰኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ብይን ፀንቷል ይፃፍ፡፡
3. ተጠሪ የሥራ መሪ እንጅ ሠራተኛ ባለመሆኑ ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/1996 በአዋጅ ቁጥር 494/1998 እንደተሻሻለ የሚታይ አይደለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ታህሳስ 30 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ